# የመርሃ ግብር መመሪያ (ፖሊሲ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

***ተዛማጅ መመሪያዎች/ደንቦች፡-*** ACA, ACF, ACH, ACH-RA, GCC-RA, GKA-RA, JHC, JHC-RA

***ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-*** Chief of Districtwide Services and Supports; Human Resources and Development

## የ MCPS ሠራተኞች ጾታዊ ትንኮሳ

A. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል (MCPS) ንብረት ላይ ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከልከል።

የ MCPS ሰራተኞች ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳን እንዲገነዘቡ፣ እንዲያውቁ፣ እንዲከላከሉ እና የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ለመርዳት የተነደፉ የሙያ ትምህርት እና የትምህርት መርሃ ግብሮች እንዲዘጋጁ ለማድረግ።

የጾታዊነት/ወሲባዊ ትንኮሳ ቅሬታዎችን ለመፍታት ውጤታማ የአሠራር ሥርዓቶችን ማዕቀፍ ለማቋቋም።

B. **ጉዳይ**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ከዚህ በታች እንደተገለፀው ማንኛውንም ዓይነት፣ ወይም በሠራተኞች፣ በተማሪዎች ወይም በሦስተኛ ወገኖች በማንኛውም ሁኔታ የጾታ ትንኮሳን አይታገስም። በዚህ ፖሊሲ ዓላማ መሠረት የ MCPS ንብረት ማለት በ MCPS ባለቤትነት ስር የሚገኝ ማናቸውም ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ፋሲሊቲን ጨምሮ የ MCPS አውቶቡሶች እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች እና በተቋሙ ባለቤትነት የተያዙ ወይም የሚንቀሳቀሱ መሬቶችን ጨምሮ ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም ማለት ነው፤ እና/ወይም በ MCPS የተደገፈ ማንኛውም ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ፣ ይህም MCPS የሚያስተዳድራቸውና የሚቆጣጠራቸው ቦታዎች፣ ሁነቶች ወይም ሁኔታዎች እና የተጠረጠረው ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ ተፈጽሟል የተባለውን ቦታና ሁኔታ ያጠቃልላል።

2. ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሶስተኛ ወገኖች ከጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ቦርዱ ሁሉም ሰዎች ከሁሉም ዓይነት የጾታ/የወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት ነፃ የሆኑበትን የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እና ለመጠበቅ እናም ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ባህሪ ለመከላከል፣ እርማት እና የዲስፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ነው። ይህንን ፖሊሲ ለማስፈጸም በቦርዱ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከቦርድ ፖሊሲዎች፣ ከ MCPS ደንቦች እና ከስቴትና ከፌዴራል ሕጎች ጋር የሚጣጣሙ ይሆናሉ።

3. ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ ማለት የ 1964 የሲቪል መብቶች ሕግ አንቀጽ VII፣ በ 1972 እና በ1991 የተሻሻለውን የህግ አንቀጽ መጣስ ሲሆን አንዳንድ አይነት የሠራተኞች፣ የተማሪዎች እና የሶስተኛ ወገን የጾታዊ/የወሲባዊ ትንኮሳዎች የ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች አንቀጽ IX (Title IX) የሚጥስ ሊሆን ይችላል።አንዳንድ የጾታዊ/የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነቶች የወንጀል ቅጣትን የሚያስከትሉ የወንጀል ድርጊቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

4. ከዚህ በታች እንደተገለጸው በአንዱ ወይም በሁለቱም የሕግ መመዘኛዎች መሠረት በአንድ ግለሰብ ላይ ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ-ጥቃት ሊፈጸም ይችላል።

a) ወሲባዊ ትንኮሳ ልክ በሥራ አቀጣጠርና በሥራ ምደባ ላይ እንደሚደረግ አድልዎ፥ በአንድ ሰው ላይ ያልተፈለገ ወሲባዊ መነካካት፣ የወሲብ ውለታ ጥያቄዎች፣ እና ሌሎች ወሲባዊ ባይርይ ያላቸው የቃል ወይም የአካላዊ ድርጊቶች ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የወሲብ ትንኮሳ ነው –

(1) እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት መቀበል በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ የግለሰቡን የሥራ አቀጣጠር ሁኔታ የሚመለከት (ማለትም፣ quid pro quo እከከኝ/ልከክህ(ሽ) ወሲባዊ ትንኮሳ ነው) ፣ ወይም

(2) በግለሰብ ደረጃ እንዲህ ዓይነቱን ባህርይ መቀበል ወይም አለመቀበል በግለሰቦች የሥራ አቀጣጠርና ምደባ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ናቸው፤ እና/ወይም

(3) እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በግለሰብ የሥራ ክንውን ላይ ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ ጣልቃ የመግባት ወይም የሚያሰጋ፣ ጥላቻ ወይም መጥፎ የሥራ አካባቢን የመፍጠር አዝማሚያ አለው።

b) በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት ፖሊሲ እንደተደነገገው አንድ ሰው ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ካጋጠመው ወይም ካጋጠማት ድርጊቱ በ Title IX መሠረት በጾታ ትንኮሳ እርምጃ የሚያስወስድ ይሆናል።

(4) አንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተቀጣሪ ለ MCPS ድጋፍ ሠጪ ሠራተኛን ለመርዳት፣ ለመጥቀም፣ ወይም በ MCPS አገልግሎት ለመስጠት ያልተፈለገ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ተሳትፎ እንደቅድመ ሁኔታ የሚጠይቅ ወይም የምትጠይቅ ከሆነ(ች)፣ ወይም

(5) በ Title IX ደንቦች ውስጥ እንደተገለጸው በቅሬታ አቅራቢ ላይ በ MCPS ትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዳይሆን ወይም እንዳትሆን እና እኩል ተደራሽነት እንዳይኖረው ወይም እንዳይኖራት የሚከለክል በጣም ከባድ፣ ጥቃት እና ተጨባጭ አጸያፊ የሆነ ተቀባይነት የሌለው ስነ ምግባር ቅሬታ በቀረበ(ባ)ት ሰው አማካይነት MCPS በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች፣ ክስተቶች ወይም ሁኔታዎች ወሲባዊ ትንኮሳ የሚከሰትበት ሁኔታና ተቀባይነት የሌለው ስነምግባር፤ ወይም

(6) በዩናይትድ ስቴትስ የጾታዊ ጥቃት ድንጋጌ የሚገለጸው "ወሲባዊ ጥቃት" ፣ "በፍቅር ጓደኝነት ሲወጡ የሚፈጸም ጥቃት" "የቤት ውስጥ ጥቃት" ወይም "እያደፈጡ ወይም እያደቡ መከታተል ወይም ማሳደድ" ነው።

(7) ሶስተኛ ወገን ማለት ከ MCPS ሠራተኞች ሌላ በእንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉ ወይም በ MCPS ንብረት ላይ የሚገኙ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ሊያካትት ይችላል፣ ነገር ግን በዚህ ባይገደብም ከ MCPS ሠራተኞች ወይም ተማሪዎች ጋር የሚገናኝ ማንኛውም ሰው ማለት ነው። በ MCPS ንብረት ላይ የሚገኙ አማካሪዎች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ ተቋራጮች፣ ኮንትራክተሮች፣ አሰልጣኞች እና ሌሎች ሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች።

## C. አቋም

1. የፖሊሲው ጥሰቶች የስቴት ወይም የፌዴራል ሲቪል እና/ወይም የወንጀል ሕጎችን የሚጥሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው እያንዳንዱ ሰው የወንጀል ቅጣቶችን የሚያስከትል መሆኑን ስለ ድንጋጌዎቹ በማሳወቅ ረገድ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ-እንድታደርግ ታዘዋል።

2. ይህ ፖሊሲ በ MCPS ሰራተኛ ወይም በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ ወሲባዊ ትንኮሳ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል። በሠራተኞች፣ በሶስተኛ ወገኖች ወይም በተማሪዎች የተፈጸሙ ክስተቶችን ይመለከታል።

3. በማንኛውም ሰው ላይ አንድ ጊዜ ወይም በተደጋጋሚ ክስተቶች ወሲባዊ ትንኮሳ ሊከሰት ይችላል።

4. አንድ ሠራተኛ ወይም ሦስተኛ ወገንን ያካተተ የወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርት በማንኛውም ሰው፣ የወሲብ ጥሰት ያጋጠመው ሰው፣ ወይም ወሲባዊ በደል ሊከሰት ይችላል የሚል መረጃ ያለው ሶስተኛ ወገን ወይም ተመልካች አማካይነት ሊደረግ ይችላል። ሪፖርቱ በአካል፣ በስልክ ወይም በኢሜል በሪፖርት አቀራረብ እና በምርመራ ሂደት እንዲሁም ከሠራተኛ ድጋፍ መርሃ ግብር (EAP) ለሚገኙ ሌሎች የድጋፍ እርምጃዎች ለሚመራቸው የሰራተኛው(ዋ) ሱፐርቫይዘር ሊሰጥ ይችላል። እንዲሁም ለሰብአዊ ሪሶርስ እና ልማት ጽ/ቤት፣ ለስነ ሥርአት ማስከበር እና ምርመራዎች ዲፓርትመንት የኢሜል ቋት በ DCI@mcpsmd.org ላይ ሪፖርት ሊደረግ ይችላል፤ ወይም የ Title IX ወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርት ማድረጊያ የኢሜል ቋት TitleIX@mcpsmd.org ሪፖርቱን መላክ ይቻላል።

   a) አቤቱታው የሚቀርብበት ጉዳይ የአቤቱታ አቅራቢው(ዋ)ን ሱፐርቫይዘር የሚመለከት ወይም ከቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ጋር የሚገናኝ ባለሥልጣን ላይ ከሆነ ሠራተኛው ቅሬታውን ለሠራተኛ ተሳትፎ፣ ስነስርአት ማስከበር እና ምርመራዎች ክፍል ሊያቀርብ ይችላል። ሪፖርቱ መዘጋጀትና መቅረብ ያለበት በ "MCPS ደንብ GKA-RA" ላይ የተገለጸውን የአስተዳደራዊ ቅሬታ አቀራረብ ሒደት በመከተል ይሆናል አስተዳደራዊ አቤቱታ - Administrative Complaint።

   b) የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ወይም በሌላ መንገድ የወሲብ ትንኮሳ ሪፖርት ማድረጉ ሆንተብሎ የሐሰት ሪፖርት ካልሆነ በስተቀር በሠራተኛው(ዋ) የሥራ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ አያስከትልም ወይም የሠራተኛውን የወደፊት የሥራ ዕድል አይጎዳውም።

   c) በሠራተኛ ላይ ወይም በሦስተኛ ወገን ላይ የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታ በማቅረቡ(ቧ) ምክንያት የበቀል እርምጃ አይወሰድበ(ባ)ትም።

   d) በተጨማሪም ቅሬታ ባቀረበ ሠራተኛ ወይም በምርመራው ሂደት ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ጣልቃ ለመግባት፣ ለመገደብ፣ ለማስገደድ፣ ለማስፈራራት፣ ለማዋከብ ወይም ለማድላት የሚሞክር ማንኛውም ሰው የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

5. በሠራተኞች እና/ወይም በሦስተኛ ወገን ላይ የወሲባዊ ጥቃቱ የተፈጸመው በሠራተኛ፣ በሦስተኛ ወገን እና/ወይም በተማሪ አማካይነት ከሆነ፤ የወሲብ ትንኮሳው በሰብአዊ ሀብትና ልማት ጽ/ቤት - የሠራተኛ ተሳትፎ ስነ ሥርአት ማስከበር እና ምርመራ ክፍል፣ በዲስትሪክቱ ጽ/ቤት እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍ አገልግሎቶች በሚሰጥ ክፍል - የተማሪ ደህንነት እና ስነ ስርዓት ማስከበር እና በስቴት እና በፌዴራል ህጎች መስፈርት መሠረት ይሆናል።

   a) የሰራተኞች እና የሦስተኛ ወገኖች የወሲብ ትንኮሳን ጨምሮ MCPS የምርመራዎችን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ አስተማማኝ ጥረቶችን ያደርጋል። ቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ስም-ሳይገለጽ ሪፖርት ቢቀርብ እንኳ፣ MCPS ሁሉንም የወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ እና መደበኛ የቅሬታ አቀራረብ መጠየቅ፣ ቅሬታዎችን መመርመርን እና ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት እርምጃዎችን ጨምሮ አግባብነት ያለው እርምጃ ይወስዳል።

   b) MCPS የአቤቱታ አቅራቢው(ዋ)ን፣ የምስክሮችን፣ እና ቅሬታ የቀረበበ(ባ)ትን ግለሰብ ሚስጥር ለመጠበቅ፣ ከ MCPS ሕጋዊ ግዴታዎች እና የወሲባዊ ትንኮሳ ክሶችን ለመመርመር እና የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለመውሰድ ከሚኖረው ጠቀሜታ አንጻር ሚስጥራዊነቱን ይጠብቃል።

6. የተጠረጠረው ድርጊት የወሲብ ትንኮሳ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን፣ MCPS ሪኮርዱን በጥቅሉ እና ሁኔታዎቹን በሙሉ፣ የባህሪውን ዓይነት እና የድግግሞሽ ሁኔታ፣ ሁኔታው የተከሰተበትን ሁኔታና ይዘት፣ የሁኔታውን ክብደት፣ የሚያሰጋ አካላዊ ጉዳት እንዳለ ወይም አዋራጅ ድርጊት መፈጸሙን፣ወይም በንግግር ብቻ መሆኑን ይመረምራል። እነዚህ ምክንያቶች ከእውነታ ይልቅ በግል ሃሳብና ስሜት ላይ የተመሰረቱ

እና/ወይም ተጨባጭ መሆናቸውን ይገመገማሉ፣ ድርጊቱ በአቤቱታ አቅራቢው ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ ብቻ ሳይሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅእኖ ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመገማል። ውሳኔ የሚወሰነው ከእውነታዎች፣ እንደየጉዳዩ በማስረጃ የመረጋገጥ ቅድመ -ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ይሆናል።

7. ሰራተኞች ድርጊቱ በተለይ ለማዋከብ ወይም ለማድላት የታሰበ ባይሆንም ለተግባራቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ ማወቅ አለባቸው።

   a) አፀያፊ ድርጊት፣ አፀያፊ ቀልዶችን፣ ነውረኛ ቀልዶችን፣ ወይም ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ የስም መጥራትን፣ አካላዊ ጥቃቶችን ወይም ማስፈራሪያዎችን፣ ማስፈራራት፣ ፌዝ ወይም ማሾፍ፣ ስድቦችን ወይም ማዋረድ፣ አስጸያፊ ነገሮችን ወይም ስዕሎችን እና በሥራ ወይም በት/ቤት ሥራ አፈፃፀም ላይ ጣልቃ መግባት የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል።

   b) ጠባይ ወይም ድርጊቱ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተገለጸው መሠረት ስለ ወሲብ ትንኮሳ የተሟላ ትርጉም ባያሟላም፣ ሌሎች ሕጎችን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን እንዲሁም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ሥነ ምግባር ደንብ ሊጥስ ይችላል። እና ሌሎች የሚጠበቁ የስነምግባር መመዘኛዎችም በዚህ መሠረት ይስተናገዳሉ። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ማንኛውም ነገር ተገቢ እና ከህግ ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ ሌሎች የቦርድ ፖሊሲዎች ወይም የ MCPS ደንቦች በመጣሳቸው ምክንያት የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃን ለመገደብ የታሰበ የለም።

   c) ማንኛውም የ MCPS ሠራተኛ የተማሪው(ዋ) ዕድሜ ምንም ይሁን ምን፣ ከ MCPS ተማሪ ጋር በፍቅር ወይም በወሲባዊ ግንኙነት መሳተፍ ወይም መሞከር የተከለከለ ነው፤ ወይም እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት ለማስተዋወቅ የተነደፈ በማንኛውም ምግባር ውስጥ መሳተፍ የተከለከለ ነው። የተከለከሉ ባህሪዎች በዚህ ብቻ ባይገደቡም በ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ሥነ ምግባር ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩ ሥነ ምግባር የጎደለው ምግባር ምሳሌዎችን ያካትታሉ።

8. ከጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የ MCPS ሰራተኞች መመሪያ፣ ድጋፍ መሻት እና/ወይም ችግሩ የሚፈታበትን ስልት ማቀንቀን አለባቸው። የሰው ኃይል እና ልማት ቢሮ - የሰራተኛ ተሳትፎ፣ ስነ ስርአት ማስከበር እና ምርመራ፣ እና የሰራተኞች ድጋፍ መርሃ ግብር (EAP) እነዚህን አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

D. **ተፈላጊው ውጤት**

1. ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወሲባዊ ጥቃቶችን ሪፖርት ማድረግ እንዲችሉ ይማራሉ።

2. ሪፖርት ስለማድረግ፣ ስለ ምርመራ፣ ምላሽ ስለመስጠት እና የድጋፍ እርምጃዎችን ስለመውሰድ ውጤታማ እና ሕጋዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

3. የ MCPS ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሶስተኛ ወገኖች ከወሲባዊ ጥቃት ነፃ በሆነ አካባቢ ይሠራሉ ይማራሉ።

E. **የአተገባበር ስልቶች**

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፦

   a) የዚህን ፖሊሲ አፈፃፀም እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን እና ደንቦችን ለማስተባበር የ Title VII እኩል የቅጥር ዕድል ኦፊሰር እና የ Title IX አስተባባሪን ይሰይማል፣

   b) የቅሬታ አፋጣኝ እና ፍትሃዊ መፍትሄን እና እንደ አግባቡ የድጋፍ እርምጃዎችን የሚሰጡ የምርመራ ሂደቶችን ጨምሮ Title VII እና Title IX ጋር በሚጣጣም መልኩ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር ደንቦችን ያዘጋጃል፣

c) ለ MCPS ሠራተኞች ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችልና የሚደግፍ ሙያዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

(1) የዚህን ፖሊሲ ተገቢ አፈፃፀም ለማረጋገጥ ለሁሉም ሠራተኞች ዓመታዊ የግዴታ ሥልጠና መስጠት፥ እና

(2) በ MCPS ንብረት ላይ ኃላፊነት የተሞላበት ባህሪ እና ተገቢ ስነምግባር እንዲኖራቸው ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች ግልጽ መመዘኛዎች እና ለሌሎች የሥነ ምግባር ደንቦች እና ሌላ መመሪያ መስጠት።

2. ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ማንኛውም የ MCPS ሠራተኛ በተገቢው የድርድር ስምምነቶች መሠረት ለፈጸመ(ች)ው ጥፋት ምላሽ የሚሰጥ ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል። የዲሲፕሊን እርምጃው በዚህ ብቻ የሚገደብ ባይሆንም የቃል ወይም የጽሑፍ ተግሳጽ፣ እንደገና ምደባ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፣ ከሥራ ማገድ ወይም ሥራ የማቋረጥ እርምጃ ሊያካትት ይችላል።

3. ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ-የምትጥስ ማንኛውም ተማሪ በ የ MCPS የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ መሠረት ለጥፋቱ(ቷ) ምላሽ በሚሰጥ ደረጃ ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰዳል።

4. አንድ ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ በዚህ የተገደበ ባይሆንም፣ የወሲብ ጥቃትን ጨምሮ Title VII የመጣስ ጥርጣሬን ለአሜሪካ እኩል የሥራ ዕድል ኮሚሽን (EEOC) አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። አንድ ሠራተኛ ከ EEOC ጋር ቅሬታ ከማቅረቡ በፊት ወይም በኋላ ለ MCPS አቤቱታ ማቅረብ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

U.S. Equal Employment Opportunity Commission
EEOC Public Portal ([https://publicportal.eeoc.gov/](https://publicportal.eeoc.gov/)); ወይም
Baltimore Field Office
GH Fallon Federal Building
31 Hopkins Plaza, Suite 1432
Baltimore, MD 21201

5. በማንኛውም ጊዜ Title IX ስለመጣስ ጥርጣሬ ሠራተኛ ለዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ ለሲቪል መብቶች ቢሮ (OCR) ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights የዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣ የሲቪል መብቶች ጽ/ቤት
OCR ኤሌክትሮኒክ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ
([http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html](http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html))፣ ወይም
U.S. Department of Education, Office for Civil Rights
Lyndon Baines Johnson Department of Education Building
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-1100

6. በማንኛውም ጊዜ የሚጠረጠር የወሲባዊ/ጾታዊ ጥቃት ባህርይ ያላቸውን ወንጀሎች ሠራተኛ በቀጥታ ለሕግ አስከባሪዎች ሪፖርት ማድረግ ይችላል/ትችላለች።

Montgomery County Policy Department
Special Victims Investigation Division
100 Edison Park Drive
Gaithersburg, MD 20878

F. **ግምገማ እና ሪፖርት**

1. በዚህ ፖሊሲ ድንጋጌ መሠረት የወሲብ ትንኮሳ ክስተቶች እና ሌሎች ስነ ስርአት የማክበር ግድፈቶችን በሚመለከት ሱፐርኢንተንደንቱ(ቷ) በየሩብ ዓመቱ ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች። የክስተቱ ሪፖርቶች ካለፈው ሩብ ዓመት ጀምሮ የተፈጸሙ ተከታታይ ክስተቶችን መረጃዎች ማካተት አለባቸው። ስነ ሥርአት የማክበር ሪፖርቱ ላይ ቅሬታ እና የመፍትሄ ሂደቶችን፥ ግምገማዎችን እና ማሻሻያዎችን፥ የስልጠና ስታቲስቲክስ እና የጊዜ ሰሌዳዎች፥ በሁሉም የ MCPS ትምህርት ቤቶች፣ ቢሮዎች እና የሥራ ቦታዎች ውስጥ የሥራ አከባቢዎች ቀጣይ ግምገማ እና ለዚህ ፖሊሲ ስኬታማ ትግበራ አግባብነት ያላቸው በ MCPS የታቀዱ ወይም የሚከናወኑ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች መካተት አለባቸው።

2. ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሠረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ክለሳ ይደረግበታል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. §2000e et seq; Title IX of the Education Amendments of 1972, 20 U.S.C. §1681 et seq; 29 C.F.R. §1604,11; 34 C.F.R 106.30(a); Annotated Code of Maryland, Education Article, §6-104, §6-113, §6-113.2, §7-303.1, §7-424, §7-424.1, §7-424.3, and §11-60; Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20, Human Relations; Code of Maryland Regulations §13A.12.05.02; Student Code of Conduct in MCPS; MCPS Employee Code of Conduct; MCPS Guidelines for Student Gender Identity

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** አዲስ ፖሊሲ፣ በሥራ ላይ የዋለው በውሳኔ ቁጥር፡- 323-21 ጁን 29/2021 ነው።